# “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” ሂሳዊ ቅርበት

ከአብደላ ዕዝራ | አዲስ አድማስ፣ 2016

ስለ አዳም ረታ ልቦለድ ውበትና ጥልቀት በመጠኑ ነው የተነካካው። ከደራሲው ጋር በተደረገ ውይይት እና በጥቂት የጥናት ወረቀቶች በአመዛኙ ስለ አጻጻፍ ይትበሃልና ዘዬ ነው የተተኮረው። <እቴሜቴ ሎሚ ሽታ> ሰባት ትረካዎች ያስነብበናል፤ ስድስቱ ሆላንድ ሳለ ነው የተፈጠሩት። (1987) በገፅ መጠን “መች ትመጣለህ?” አጭር ልቦለድ ነው፤ የተቀሩት እንደ novella እምቅ ናቸው። ሰባቱም ብርቅ ትረካ ስለሆኑ፥ እያንዳንዱ የግሉን ኮስታራ ቆይታ ይማጠናል። ይህ ሂስ-ቀመስ ጽሑፍ፥ ሀምሳ ገፅ በፈጀ የስብስቡ ርዕስ በሆነው “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” ላይ ብቻ ያተኩራል።

ከዚህ ልቦለድ የተወሰኑ ገጾች ተመርጠው የዘመኑን መንፈስ -zeitgeist- በተለይ በገፀባህሪይዋ ምስራቅ ህይወትና እንግልት ላይ ባሳደረው የልቡና ወረራ ላይ ያጠነጠነ የአብረሃም ገዛኸኝ ፊልም ተሰርቷል። “ሃሜት፥ ጥላቻ፥ ውሸትና ቅናት የሞራል ወንጀሎች ... ከግለሰብ አልፈው ... ሀገር የማፍረስ አቅማቸው” በፊልሙ ተስተውሏል። ትረካው ግን የዘመን መንፈስ ክስተቶች ውጤት አይደለም። የግለሰብ ማንነት አቅምና ረግረግነት፥ ብሎም የልጅነት ዳራ የጐልማሳን ዛሬነት ሲቧጥጥ፥ ሰው ለራሱም ለሌላውም ሰቆቃ ይሆናል።  ለማኅበረሰቡ እምነት ግለሰብ ሲገዛ -እንደ ታደሰ- እንግልት የሸሸገ ሰላም እስከ መላበስ ድረስ ትረካው ይፍታታል። የዶክተር በድሉ ዋቅጅራ ልዩ አሻሚ መንቶ ምስራቅ እና ሎሚ ሽታ ይነጠቁበታል።

“እኔ ምኑን ተጐዳሁ፥ ላንቺ ይብላኝልሽ እንጂ፤

እንደ መንፈስ ውስጤ ሳኖርሽ፥ አካል ሆነሽ ስትሄጂ”

እንደ ስዕል የመንፈስ ቢጋር ውስጥ መታጠር የመረጠችው ምስራቅ፥ መቃኑን ነቃቅላ አካል ሆና ነፃ ከወጣች ሎሚ ሽታ እኩል ተቀርፀዋል።

ከጭብጦች አንዱ የሆነው የሰዋዊ ግንኙነት ረቂቅ ገፅታዎች፥ በተለይም የወንድ-የሴት ሰበቃ እስከ ውስጣዊ ሥነልቦናዊ ጓዳ የመጥለቅ ምትሃት፥ አዳም ረታ ተክኖበታል። የስምንት ሴቶች ልቦለድ (143 ገፅ የፈጀው) <ኩሳንኩስ> በተመስጦ ሲነበብ የሀዲስ ዓለማየሁ ስብለወንጌል፥ የበዐሉ ግርማ ሉሊት፥ ተሻግሮም የቶልስቶይ ገፀባህሪ አና ካሬኒን ... ይደበዝዛሉ። ይህ <ይወስዳል መንገድ፥ ያመጣል መንገድ> መጽሐፍ ውስጥ ያደፈጠው <ኩሳንኩስ> ወደፊት በሂሳዊ ንባብ ባባብለውም እነሰናይት፥ እትዬ ወርቄ፥ ሣራ ... ከምናቤ አይሰክኑም፤ እየተንጓለሉ ሰርክ እበረግጋለሁ። ከሰው ለላቀ ገፀባህሪ መደንገጥ ምን ይደንቃል? ዋሲሁን በላይ በአርምሞ አግኝቶታል።

ትበረግጋለች ነፍሴ በትንሽ ኮሽታ፤

ሠቀቀን ገደላት ጊዜው ላይ ተኝታ”

ዝነኛው ባለቅኔ Ezra Pound ስለግጥም አጻጻፍ የመሰከረው ለአዳም ረታ የቋንቋ ጥበብ ይመጥነዋል። “Great literature is simply language charged with meaning to the utmost possible degree.”  የአብይ ሥነጽሑፍ አስኳል በትርጓሜ፥ በአንድምታ የተለበለበ ቋንቋ ነው እንደማለት። ጥቃቅን ግን ሌላው ግለሰብ ሊመሰጥበት ቀርቶ ልብ የማይለውን ምስል፥ እንቅስቃሴ ወይም የሆነ ድርጊት የአዳም ረታ ብዕር ሲፍቀው፥ ሲያሻሸው የሚፈልቅለት ውበት-አስቀያሚነት እስከ ፍፁም ንዝረት፥ እስከ አስደንጋጭ ግርምት ይረቃል፤ እሳቦትና ምናባችን ይታመሳሉ። ለአዲስ በኩር ክስተት አሁንም እንበረግጋለን። (በአስረጅ እመለስበታለሁ)።

አዳም፥ በኑሮ ውጣ ውረድ ተጠምደው ሲያቃስቱ፥ ሲቦርቁ ገፀባህሪያት ቀረፀ እንጂ አንዱን እኩይ፥ ሌላውን በጐ በማለት አይፈርድም። አንባቢ ነው እንደ ብስለቱ፥ እንደ ገጠመኙ የባለታሪኮችን ህይወትና አቋም የሚመነዝረው።

ለዚህም ነው ሎሚ ሽታ ለአንዱ አርአያ እንስት ስትሆን፥ ሌላው የሚያወግዛት። ደራሲው በገፀባህሪያት ድርጊት ሳይታቀብ ውስጠታቸውን ሲቦረቡር ገለጣው ስዕሉ ያስደምማል። አንድ መነኩሴ ለመምህሩ ያቀረበው ጥያቄ ያታወሰኛል። ስለ ስዕል የሚያትት መጽሐፍ ነው። “ብርሃን ማጤን፥ ጥላውን መሳል” ከሚል ምዕራፍ የተተረከ ነው።

እኔ ምንድነኝ?” ብሎ ጠየቀ መነኩሴው።

መምህሩም መለሰ፤ “ከውስጥህ ያደባ ድብቅ ነገር አለ። ዘልቆህ የተሸሸገውን እንቅስቃሴ መላመድ አለብህ።”

መነኩሴው እውስጡ ስለተሰወረው ነገር እንዲብራራለት ተማጠነ። መምህሩ በሃሳብ ከነጐደ በኋላ ዞር ብሎ መነኩሴውን አስተዋለና አይኑን ገለጥ፥ ጨፈን ብቻ አድርጐ ሄደ። ይህን ድርጊት -አይንን መጨፈንና መግለጥ- የመሰለ አፍታ መፈልፈል የሚችለው፥ ለፈጠራ ድርሰት የሚያበቃው አዳም ረታ ብቻ ነው። “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” ን በማዟዟር የተለያየ ገጾቹን በጥቂት ክፍሎች ለማንበብ እሞክራለሁ።

## መገለል

“ለስራ ወጥቶ ሲገባ ቀድሜው ከደረስኩ ጊዜው አያልፍልኝም ነበር። ኮቴውን ስሰማ እተቀመጥኩበት እደነግጥ ነበር። እቆምኩበት እደነግጥ ነበር። ዛሬ ድረስ የእርምጃው ዳና እንደ ሙዚቃ እንደ ከበሮ ቃና በጆሮዬ ውስጥ አለ። ከሶስት ከአራት ሰዎች መሃል የእግሩን አጣጣል መርጬ ማውጣት እችል ነበር። የሚያስቀና መልክ የሚያስቀና ቁመና ነበረው። በአልኮል እየፋቁ በሐሰት መረጃ እየተረተሩ እስኪያጠፉት ድረስ። … ጠረኑ ልጄ ገና የተለቀመ ጥጥ ይመስል ነበር።”

(ምስራቅ ለልጇ ለታደሰ፥ ስለአባቱ ፍቅረስላሴ ካወጋችዉ የተቀነጨበ) [እቴሜቴ ሎሚሽታ ገፅ 105 ]

ምስራቅ ልጧ ትርክክ ብሎ ለፍቅረሥላሴ የተርበተበተችው ገና በአፍላ እድሜዋ ነበር።

“… ከኬክ ቤት(ብርቅ ነበር ያንጊዜ) እሱ ሲወጣ እኔ ልገባ ስል … በሩ ጋ ሳየው፥ እዚህ ልቤን መታኝ፥ የማላመልጠው ነበር። … ሌላ ሰው አስጠላኝ። ልቤ ግብት አለ። ያን ቀን ማታ ቤቴ ገብቼ ሙሉ ምሽት ሳስበው ነበር። አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተኝቼ ፈዝዣአለሁ፤ ዝም ብዬአለሁ።”

ፍቅር አሸነፋት፤ ለባሌ ዳንስ ሃንጋሪ መሄድ ስትችል ቀረች። የህይወቷን አቅጣጫ የሚገራ ትምህርት፥ በመዳፏ ያለውን ተገን አሽቀንጥራ እንድትጥል የመውደድ ሃያልነት አስገደዳት፤ ከፍቅር ጉም በዳበሳ ተሰወረች። ከፍቅረሥላሴ ትዳር ይመስርታሉ። ፍቅሯን ሳታጣጥም ገና ነፍሰጡር ሳለች ባልየው በጓደኞቹ ወሬ ተደናቅፎ እየተገለላት፥ ሰክሮ በውድቅት እቤት መመለስ ጀመረ። ፍቅረሥላሴ የረባ ስራ ነበረው። የተለያዩ ወንዶች ተኝተዋት እንደነበር አወሩለት፤ ልቡ ሻከረ።

“ታድያ አባትህ ደም ስሩ ተግተርትሮ ሊፈነዳ ደርሶ ትልቅ ዕውነት ከሰማይ እንደ ወረደለት ሁሉ … `እንዴ ጨዋ ነኝ ብለሽ የለ፥ ውሸትሽ ሲወጣ ለምን አትክጂ?` ይለኛል።”

የቅድመ ትዳር ህይወቷን ነበር የሚያማው። የተወለደው ህፃን የሱን መልክ ስለወረሰ ለጥቂት ወራት ምስራቅ በፍቅር መፍካት ቻለች። ጥርጣሬው ግን አገርሽቶ ህፃኑ ታደሰ ገና ጡጦ ሳይጥል ፍቅረስላሴ ያርፋል።

“አንድ ቀን ከገነት ሆቴል ወረድ ብሎ ቦይ ውስጥ ከቁሙ ወደቀና - ያየ ሲያወራ - የተሰበረ ቆሻሻ ጠርሙስ በአንገቱ ገባ። አለቀስኩ እንጂ ሲሞት። ... ሳንደሰት፥ እሱም በልጅነቱ እኔም ገና በልጅነቴ እንዲህ ምርር እንዳለን ሁሉ ነገር አለቀ።”

ታደሰ የአባቱን ህልፈትና የጠባቸውን መነሻ  ስለማያውቅ እናቱ በምትተርክለት ብቻ አስተሳሰቡ ይቦካል።

ምስራቅ ለጥቂት ወራት አዝና ብድግ ብላ ቁዘማዋን ገፍፋ፥ አዲስ ሌላ ህይወት ለመጐንጐን አልባዘነችም። ተኮፍሳ ቀረች። በፍቅር የተሰበረ ልቧን መጠገን ተሳናት። የባሏን አሉባልተኛ ጓደኞች ጠልታ ራሷን አግልላ ማኅበረሰቡን ጭምር ተራገመች፤ አቄመች። ለነገዎቿ ከምታልም፥ ትናንቷን እየወለወለች ፈዘዘች። ታደሰን ለማሳደግ ግን በታይፒስትነት እየሰራች ዘለቀች።

“ብትረባም ባትረባም ያንድ ገፅ ያልተበረዘች እሱን የማፍቀር ታሪኬን ይዤ አፈር እገባለሁ። ወደሥራዬ ስሄድና አስቤዛ ልገዛ ካልሆነ ለአስራ ሰባት አመታት ከቤት አልወጣሁም።”

እንዴት ግለሰብ እንዲህ ሊሰበር ሊገለል ቻለ? የሰዓዳ መሀመድ አጭር ልቦለድ “የውድቅት ዕንባ” [ወንዞች እስኪሞሉ፥ 1998 ገፅ 109-127] ትዝ ይለኛል።  የሮቤል እናት ዩኒቨርስቲ የመግባት ነጥብ ብታመጣም ከድህነት ለመጠለል ትዳር ትመሰርታለች። ሆኖም የምታፍቅረው ባል ችላ ይላታል።

“የመጀመሪያ ባሌን እወደው ነበር። ግን አሁንስ እጠለዋለሁ? ታድያ የመጀመሪያ ልጄ አይኖቹ የሚረብሹኝ ለምን ይሆን? ... የኔ ኮከብ ነበር። ወጥቶ  ሲገባ በስስት አየዋለሁ። ... የብርሃኔን ገመዶች በፍቅሩ ውስጥ ነበር የፈተልኳቸው። ... ፍቅር ሀያል ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን ክህደትና ሀሰት ዘነጣጥለው በሉት። ... ፍፁም በተሰበረ ልብ ጥልቅ ሀዘንና ምሬት፥ ግን በጠራ አእምሮ ኮከቤ ሲጠልቅ ተመለከትኩ። እጅ ላለመስጠት፥ <ሰንበሌጥ የምታህል ምርኩዜን ነፋስ እንዳይወስዳት እታገል ነበርና’’

በማለት ላለመሸነፍ ተራ በተራ አራት ትዳር መስርታ፥ አራት ልጅ ወልዳ ድህነት እየመዘመዛት ዳክራለች።

መከራዋ ከምስራቅ የመረረ ነው፤ ምስራቅ ግን ምን ሰበራት? እስከ ህልፈት ተሸሽጋ እንዴት ነቅዛ ትቀራለች? አዳም ረታ የቀረፃት አለምፀሀይ [ይወስዳል መንገድ፥ ያመጣል መንገድ፥ መጋቢት 2003 ገፅ 228-235] የምታፈቅረው ባሏ ከጦር ሜዳ ሲሰዋ፥ ከሁለት አመታት በኋላ ሀዘኗን አወላልቅ ስትንቀሳቀስ፥ መኪና ገጭቷት አንድ አይኗን ብታጣም አትሸነፍም። “በቀስታ በቀስታ የተበላሸውን አይኔን መኳል ጀመርኩ። የሚያስፈራ ነገር አለው። ግን ይሄ አለመታደል እንደምታዩት ፊቴ ላይ የሰፈረውን ፈገግታ አያጠፋውም። ወጣት ነኝ። ከተማዬ ይህች አዲሳባ ገና ትያትር የማይችሉ ቆፍጣና ሴቶችና የሚመቹ ወንዶች አሉባት።” አለምፀሀይ ህይወትን ለማጣጣም ልክፈት ሲፀናወታት ምስራቅ ግን Albert Camus እንዳለው አንድ ነጠላ ቀን ብቻ የኖረ ግለሰብ፥ ለአመታት ከወህኒ ቤት ቢጣል የኑሮ ስልቹነት ተላምዶ የዚያችን ቀን ትዝታዎች ቀዶ እየሰፋ ረጅም ዕድሜ ማዝገም ይችላል። (The Outsider - Penguin 1986)

በዚህ ዝነኛ የህይወት ዘበትነት የተፈረፈረበት ልቦለድ ዋናው ገፀባህርይ Meursault በአጋጣሚ ሰው ገድሎ ከእስር ቤት ይወረወራል። ከሚያውጠነጥናቸው  ጉዳዮች ይህ የአንድ ቀን ትዝታ፥ ስንቅ ሆኖ ሰው ለአንድ መቶ አመት ከማኅበረሰብ ተገልሎ ሊኖርበት እንደሚበቃው፥ የህይወትን ርዝመት ከነግሳንግሱ ሊተካ የመቻሉን አባዜ ነው። I realized then that a man who’d only lived for a day could easily live for a hundred years in a prison. He’d have enough memories not to get  bored. [ ገፅ 77 ]

ያልቀዘዘ ፍቅርና የማኅበረሰብ የተጋነነ ስጋት ምስራቅን መዘመዛት። ማንም ሳያስገድዳት ተነጥላ፥የኑሮ ዘበትነትን ወዳ፥ ልጇን በጀርባዋ አዝላ ጨለማን መቆፈርና ማቡካት መረጠች። የፍቅረስላሴ ፍቅር እሷን የሰበረ፥ ታደሰንም ያመሳቀለ ምርጫ ነበር።)

ማኅበረሰቡ ገላመጠኝ፥ ተጠቃቀሰብኝ በማለት ማፈግፈጓ ድክመት ነው። በትናንቶቿ እየተከዘች ለዛሬና ለነገ ደመኛ ሆና፥ ከሌላው ላለመነካካት በፍርሃት ተሸብባ መኖሯ የልጇን የታደሰን ልቡና -psyche -ገጣጥቦታል። (ልቡና "በየጊዜው ፍቺውን እያሰፋ የመጣ፥ በአንድ በኩል እንደልባዊነት (ልብ ማድረግ፥ ማስተዋል፥ ማወቅ/በጥቅሉ አእምሮን)፥ በሌላ በኩል እንደነፍሳዊነት (እስትንፋስ ነፍስ፥ ሕያውነት) ያሉ ተዛማጅና ተወራራሽ ጽንሰ ሐሳቦችን ጠቅልሎ የያዘ ዝንቅ መጠሪያ ነው።" ቴዎድሮስ ገብሬ፥ በይነ-ዲሲፕልናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ 2001፥ ገፅ 254-255)

"ከቤት ስወጣ ወጥመድ ይሸተኛል። መርገምት በቁና ተሰፍራ እንደ ትኩስ ንፍሮ እየጤሰች የምትጠብቀኝ ይመስለኛል። ... በመንገድ ላይ ከሚተላለፉት ሰዎች የትኞቹ ባሌን አጠፉት? የትኞቹ እንዳረጅ አደረጉ?"

የሰፈር ሰው እንደ እብድ ቆጠራት እንጂ መንፈሳዊ ህመሟን አልተገነዘበም። ከልጅነት እስከ አዋቂነት የእናቱን ብሶትና ትረካ እያደመጠ፥ ይህን ስነልቦናዊ ቀውሷን እየተመገበ ታደሰ አቀረቀረ፤ እንደ እኩዮቹ ለህይወት መቦረቅ ተሳነው።

"ከናቴ ጋር መታየት አፍር ነበር። ገና የፊት ጥርሴን ነቅዬ ጣምራ ኦክሲጅን ስስብ፥ የእያሱ ልጅ `እብድ ያሳደገው`ብሎ ሰድቦኛል። ... ሜዳ ዘልቄ የማልሄድበትን ምክንያት እናቴ ታውቃለች።" ታደሰም ሰለባ ሆነ። ሰው እየራበው ከሰው እየሸሸ ትምህርቱ ላይ አተኮረ። ህግ አጥንቶ በማዕረግ ተመረቀ። ለእናቱ እንግልት ምክንያት የሆኑትን ለመቅጣት ቢከጅልም፥ ማስረጃ አልነበረውም። ልቡ እንዳቄመ እናቱም ለዘልአለም ያሸልባሉ። ለሀያ አምስት አመት በየቀኑ ተድብቃ የምታፀዳውን የሟች ባሏን ኮትና ሸሚዝ -Camus እንዳለው በትናንት ሰናፍጭ በምታክል ትዝታ ገርጥታ - ለመጨረሻ ጊዜ ተኳኩላ ኮትና ሸሚዙን ለብሳ ትሞታለች። ባልፈረጠ ፍቅርና መዘዙ ማቀቀች። ምን ብትበድል ነው ሁለት ጊዜ የሞተችው? አንዴ በህይወት ሳለች፥ አንዴ ስትቀበር።

ከዚህ የባይተዋርነት ጠጣር ዛጐል ውስጥ ያደገው ታደሰ፥ ከነሥነልቦናዊ ቀውሱ፥ ቁስሉንና ቂሙን እንደቋጠረ ነው ከዚያች ውብ ረጅም ወጣት ሎሚ ሽታ ጋር የተገናኘው፤ የተቆራኘውም። ራሱን ከአወቀ ጀምሮ እናቱን ከብቸኝነት አዘቅት ጐትቶ ለማትረፍ አልተስገበገበም። ሰውን የመሰለ - የሚፋጅና የሚቀዘቅዘውን - አገለለች፤ መቼቷን አጠበበች። በፍቅር እንደ ቆሰሉ በባዶ፥ በብቸኝነት ወራትንና እድሜን መማገድ የኅላዌ ጭካኔ ነው። ለብቻ ከመንደድ ከሌላው እየተፋተጉ መኖር ለመላላጥም ለመወርዛትም ዕድል ይለግሳት ነበር። ሳይሆን ቀረና ይህን ሥነልቦናዊ ሸክም ልጇ ታደሰ ወረሰው። ሎሚ ሽታ ምን ፈረደባት?

ይህ ልቦለድ እንደ ተነበበ አያበቃም፤ ከምናባችን ይፍታታል። አልባሌ የመሰለ ክስተት ድንቅ የኅላዌ ምስጢር እንዴት ፈላበት? ከ"እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ግላዊ ማኅበራዊ አንኳር የመፈልቀቅ ሂስ ለጊዜው ገታ አድርገን፥ በአዳም ረታ የቋንቋ ምትሀት እና የአተራረክ ጥበብ እንደመም። ፐርሺያዊ ገጣሚና ሱፊ፥ Rumi እንዳስተዋለው ለድምፅ ጋጋታ ሳይሆን ለቃላት ከፍታ መብሰከሰክ ይበጃል፤ ለአበባ ማጐነቆል ዝናብ እንጂ ነጐድጓድ መች ጠቀመው? ወጣት ምስራቅ ገና ትዳር ስታጣጥም፥ ለባለቤቷ ትማግጥ እንደ ነበር ተወራለት። እሱም ቀልቡ ተፍቆ፥ ከውስጡ የሰረገውን ሃሜት ለማለዘብ በስካር ተንገዳገደ፤ ከመንገድ ወድቆ ይሞታል። ምስራቅ ለአመታት ከማኅበረሰብ ተገለለች፤ በትዝታዋ ተሸብባ ልጇ ታደሰ ተመርቆ ራሱን ሲችል አቃስታ ለዘላለም አሸለበች። ታደሰና ሎሚሽታ ለአምስት አመት ያክል በሰማንያ ተቆራኝተው ቢኖሩም፥ የትዳር አጋሩ ሰለቻትና ለአስናቀ ልቧ ተርበትብቶ ኮበለለች። ይህ ተረት የመሰለ፥ በየመንደራችን የሰማነው በእኛና በጐረቤት የደረሰ ገጠመኝ እንዴት መሳጭ ሥነልቦናዊና ውበታዊ ጓዳ ተበረከተለት?

## ***ክፍል 2***

"እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ታሪኩ ስስ ነው። በዚህ ቀጭን የትልም ክር -plot-እየተሸለኮለከ እንደ ጉንዳን የሚርመሰመሰው የኑሮ ጣዕም (ሸንፈት፥ ፍቅር፥ ጥላቻ፥ጉጉት፥ ንዴት፥ ትዝብት ...) ያጣድፈናል። እንዴት?

የለመድነው ክስተት ትኩስነት ብኩርነት ደራርቦ ለእለት በዕለት እንቅስቃሴ መሳቀቁ፥ መንዘሩ፥ መፍካት መጠውለጉ እውስጣችን ለመስረግ ምን አበቃው? ልቦለዱን ደጋግመን ብናነብ ይህ ጥበባዊ-ግባቱ ከምን ፈለቀ? ደራሲ የሆነ እሳት ለማያያዝ ነፋስ እየፈተነው ገና ክብሪት ይጭራል። ለአዳም ረታ ግን እያንዳንዱ ቃል ረመጥ ነው፤ ለዝዞበት አያውቅም። በ"እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ኖቬላ ብንወሰን እንኳን ቢያንስ አራት ኅብረ- ቀለማት ማድነቅ እንችላለን። አንድ፥ብዕር ነው ብሩሽ እሚያሰኝ የቃላት ስዕል፥ የቋንቋ የልብ ንዝረት ረቂቅነት። ጥቃቅን ግን ሌላው ግለሰብ ሊመሰጥበት ቀርቶ ልብ የማይለውን ምስል፥ እንቅስቃሴ ወይም የሆነ ድርጊት የአዳም ረታ ብዕር ሲፍቀው፥ ሲያሻሸው የሚፈልቅለት ውበት-አስቀያሚነት እስከ ፍፁም ንዝረት፥ እስከ አስደንጋጭ ግርምት ይረቃል። ሁለት፥ መስመራዊ ከመነሻ እስከ መገቻ መተረክ ሳይሆን እንደ ድርጊቱ ክብደት የጊዜ ቅደም ተከተል ተፈርፍሮ እጅጉን የሚጐላ፥ በጣምም የሚደበዝዝ ትዕይንት ይበራያል። አዋቂን የሚያስተክዝ የልጆች ዘፈን፥ ስንኞቹ እንደ ሙዚቃ ኖታ ለትረካው ጠቋሚና ቀስቃሽ ሆነዋል። "ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ" ስንኞች ተራቸውን ይጠብቃሉ። የትረካው አቅጣጫ ሲሰበር፥ ወደ ሩቅ ትናንቶች ሲጐተት በ"ቸብ ቸብ" ይወረሳል፤ ሌላ ስሜትና እሳቦት እንዲመጥን ነው ቅኝቱ የጐረነነው።

ሶስት፥ ውጫዊ እንቅስቃሴ ሳይሆን ውስጣዊ ሥነልቦናዊ ገመናዊ ህይወትና እስትንፋስ አለርህራሄ ይጐረጐራሉ። ፍልስፍናዊ አመለካከት ይጠልባቸዋል። አንባቢ አምላክን በልቡ እያሻሸ የሚዘጋው የፀሎት መጽሐፍ ሳይሆን፥ እንደ የእንጨት ሙጫ ጭስ የሚያንሰራራ ህልም አይሉት ትካዜ፥ ብቻ መጠበብ ይጀምራል። አራት፥ የአንፃር ምርጫ -focalization- አንባቢ ከአንድ ገፀባህሪ በላይ ስለ ድርጊቱ ሆነ ያባለታሪኮቹ ምኞትና አስተሳሰብ ያውቃል። እያንዳንዱ ገፀባህሪ ያንን ተመሳሳይ ክስተት እንደ ብስለቱና ፍላጐቱ ሲተርከው የሚሰነጣጠቅ የሚፈረካከስ ጨለማ አለ። በገሀዱ ግኑኝነት ቅርፊቱን ገላውን አስተውለን ሰውን ማማትና ማሞገስ እጅጉን ስህተት መሆኑ ይጐመዝዛል። መጋረጃ ሲተረተር፥ በር ሲወላልቅ ጓዳ ጓዳው ይጋለጣል፤ መሸሸግያ ጥጋጥጉን ይቀማል። ከአዳም ብዕር የሚሰወር ገፅታ የለም፤ እሱ ግን መገሸለጥ ብቻ ሳይሆን መለበድም አይሳነውም። ነጥቦቼ ተንሳፋፊ አረፍተ ነገሮች፥ እፉዬ ገላ ብቻ እንዳይሆኑ ከልቦለዱ መጥቀስ ያስፈልጋል። ሊንድማን Thinking in Future Tense በሚል መጽሐፉ ከተራነት ብርሃንን የማንጠፍጠፍ ተሰጥኦ ደንቆታል። "One of life's most fulfilling moments occurs in that split second when the familiar is suddenly transformed into the dazziling aura of the profundly new ... patterns where only shadows appeared just a moment before." በህይወት ከእጅግ አርኪ ቅፅበቶች አንዱ፥ በዚያ ሽርፍራፊ ሴኮንድ ድንገት የተለመደው የተሰለቸው በአብረቅራቂ ፍፁም አዲስ መንፈስ መለወጡ ነው፤ ከአፍታ በፊት ልሙጥ ጥላ ብቻ የረበበበት በንድፎች ይወረራል እንደማለት። ገጣሚ-ሰዓሊ አገኘሁ አዳነ ድልነሳው "መልቲ ብርሃን" በተሰኘ ግጥሙ ብኩርነት ብቻ ሳይሆን እስከ መስመጠ ተቀኘበት። አንድ፥ ሁለት፥ ሶስት፥ ብለን ፅልመቱን ዘለልን

መብራት የጠገበ መሬት የመሰለን

የረገጥነው ብርሃን

አዘቅት ሆኖ ዋጠን።

አዳም ረታ ዛሬ አይደለም እጅጉን ረቆ ደቃቅ እንቅስቃሴ፥ ስሜት ሆነ ድርጊት ... እስከ ዕንቁነት የፈለፈለው፤ አያሌ አንባቢያንን የሚደመሙበት ክህሎት የተካነው ከመነሻው ነው። የዛሬ 33 ዓመት (1975) የደረሰው አጭር ልቦለድ "ትዝታ"(አለንጋና ምስር፥ ገፅ 22)እንደ አብነት ሊነበብ ይችላል። ዳዊት ዳጐስ ያለ መጽሐፍ ዘርግቶ ጫት እየቃመ ደንገዝገዝ ካለ የታፈነ ክፍሉ በንባብ ስሜት እንደ ሰጠመ አጐቱ አንዲት ሴት -ፍሬ ሕይወትን- ይዞ በር ገፍቶ ይገባል።

“በተከፈተው በር አጐቴና ያመጣት ሴት ያስገቡት ቀዝቃዛ አየር እንደ ማሕፀን ትሞቅ የነበረችው ክፍሌ ውስጥ ተጠቀጠቀባት”

ዝም ብሎ ማድመቂያ ምስል አይደለም። የተናጋሪው ስሜት ከንባብ ወደ ሚቆረፍድ ድባብ ሲንሸራተት እኛም ከክፍሉ የተቀመጥን ያክል ይሰማናል። በበለጠ ግን የምንፈዘው የአፍታ እንቅስቃሴ ስዕል ሲያንሰራራበት ነው።

“ደብዛዛ ብርሃን ካለበት አቅጣጫ፥ የፍሬ ሕይወት አንድ እጅ ወደ ፊትዋ እየተንሳፈፈ ሲያልፍ --የራሱ ነፃነት እንዳለው ሁሉ-- አንድ ነገር ብልጭ አለ። ደቃቃ ነገር የፈለቀ መሰለኝ። ቀለበት። የወርቅ፥ የብር ወይ የሌላ ዓይነት ብረታብረት። አንድ ጣትዋን ቅባት ነክቶት ወይም ያልደረቀ የምራቅ ነጥብ ሰፍሮበት ይሆናል። ለብቻዬ ፈገግ አልኩ።”

ይህን የአፍታ እንቅስቃሴ የፊልም ካሜራ እንኳን ይስተዋል። የቀለበትና ምራቅ መተካካት እንስቷ ለድሪያ መፍቀዷ በኢ-ንቁ አእምሮው የደባበሰው ሽርፍራፊ ስሜት። ከምንም ብዙ መፈልቀቅ መች አዳም ተሳነው? ስለሴት እጅ አንድ ብልጭታ ልድገም። ከ12 ዓመት በፊት በ“ኩል” ንዑስ ርዕስ የደረሰው ትረካ ነው። (ይወስዳል መንገድ፥ ያመጣል መንገድ፥ ገፅ 223) የባለቤቷ ትዝታ ያፈናት ዓለምፀሐይ የተመሰጠችው በምንም ነው ማለት ይቻላል።

“ትቼው ከአውቶቡስ ከመውረዴ በፊት እጇን ጐትቶ ህዝብ እያየ (ይታያችሁ በዚያ ግፍያ መሃል) ይስመዋል። ብዙ ጊዜ አይበሉባዬ ላይ እርጥበት ይሰማኛል። አንዳንዴ በነገሩ ልቤ ባብቶ መንገድ ላይ ሰው እንዳይታዘበኝ አድርጌ ሳልታይ አይበሉባዬን እስማለሁ። በከንፈሮቼ መሃል ምላሴን ብዙ ሳላሳልፍ አውጥቼ የተወልኝን የአፉን ወዝ እልሳለሁ። እንዴት ደስ እንደሚለኝ። ይህችንም ደስታዬን አብራኝ ለምትሰራ ልጅ ስነግራት ምን አለች መሰላችሁ? ከት ከት ከት። በቃ ከት ከት። ተሳስቼአለሁ? ወይስ ቀንታ ነው? ወይስ ዞሮባት ነው? መልሱን ፍለጋ አልባዘንኩም’’

ጥቃቅን ግን መሳጭ የመግለጥ ተሰጥኦ ቢሆንም፥ አዳም በምናቡ ይህን እንዴት ማየት ቻለ እያሰኘ ነፍስ ይዘራበታል። ይህ ምስል ከልቦለዱ እሴት ጋር ሲፋተግ እኛም -አንባቤ- ራሳችንና አካባቢያችን ትክ ብሎ የመመልከት አቅም ይቀሰቀስብናል። ለሂስ ወደ ተመረጠው “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” እንመለስ።

“ከተቀመጠችበት ተነስታ ጓዳ ገባች። በመኝታ ቤት መስኮት መጨለም ወደ ጀመረችው የአዲስአባ ሰማይ አያለሁ። ነጭ የደመና ብጣሽ ግራጫ ሰማይ ላይ በምስማር እንደ ተመታ ሁሉ ቀጥ ብሏል። እናቴ ከጓዳ የከሰል ምድጃ ይዛ ወደ ሳሎን አለፈች። እንድመጣ ጠራችኝ። ሰማይ ላይ ሳፈጥ ቆየሁ። ሳሎን ስገባ ከሰል ምድጃው ላይ ጀበና ተቀምጧል። የምድጃው ፍም ተንገልጧል። ሶፋ ላይ ስቀመጥ አስራ ሁለት ሲኒዎች የሸፈኑት የእንጨት ረከቦት መጣና ከእግሬ ትንሽ ራቅ ብሎ ተቀመጠ። ከዛ ጐን ከዕጣን ማንደጃ ላይ እየተከዘ የሚነሳ የመላዕክት ጅራት የመሰለ ጭስ” [ገፅ 104]

ታደሰ ከሎሚ ሽታ የመሰረተው ትዳር ፈርሶ፥ ስለ አለፈ ህይወቱ በምልስት ሲተርክ እንዴት ይህ አዕምሮ ውስጥ ሊቀር የማይችል ትዕይንት ፈካለት? አሁን እየተፈፀመ ያለ ትኩስነት፥ ከአመታት በፊት የተደረገ የተፋቀ ትዝታ ባለመሆኑ አዳም ዛሬና ድሮ ተቀላቀለበት? ጊዜ እንደ ጠጅ ከብርሌ እየዋለለ እንዳሻን መዳፋችን ላይ አንጠባጥቦን የምንልሰው የታሸገ ፈሳሽ ነው ወይ? ተራኪው ሥነልቦናዊ እንግልት እየመዘመዘው ሳለ ይህ ጊዜ ያደበዘዘው እንቅስቃሴ እንደ የመጀመሪያ ፍቅር በጥራት ይታወሰዋል? የተደረገ ነው ወይስ ዛሬ ከምናቡ ፈጥሮ እየዋሸን ነው? ወዘተ... ቢያሰኝም ስናነበው የገለጣው ጥበባዊ ውበት ያፈዝናል። ሰማይ ላይ በሚስማር የተመታ ደመና፥ ከዕጣን ማንደጃ እየተከዘ የሚነሳ ጭስ ዘይቤው ቅኔን ያደናግዛል። “መከርኩ። አስመከርኩት። በዕንባዬ ለመንኩ። እምቢ አለ። `እምቢ` የምትለው ቃል ከንፈሮቿ ላይ ስትፈነዳ የተፈናጠረ ደቃቅ ምራቅ

አፍንጫዬ ላይ ሲያርፍ ተሰማኝ። አልጠረኩትም። ዐይኖቼን ጨፈንኩና ረቂቅ ቅዝቃዜውን በቆዳዬ ጠጣሁ። እናቴን እወዳታለሁ።”[ገፅ፥105]

የእናትን ፍቅር ከምራቅ ፍንጣሪ ማጠለል የአዳም ብርቅና ልዩ ችሎታ ነው፤ የጊዜን ፍሰት በዕውነታ ህግጋት መዳኘት፥ ዛሬ ነው ወይስ ያረጀ ትናንት ብሎ ለመብሰክሰክ የማይፈቅድ ረቂቅነት ነው። ሎሚ ሽታ ከባለቤቷ ታደሰ እየተላቀቀች ልቧ ለአዲስ ወንድ ሲንሸራተት ትረካዋ ይመስጣል።

“ ... ኈኑ ተጋድሜ ገና ሳገባው አደርገው እንደነበረ ሁሉ ሆዱን እዳብስለታለሁ፥ ችፍ ያለ ቅንድቡን በአመልካች ጣቴ እካክክለታለሁ፥ በጅልጃላ ውስጥ ሱሪው ስር እጄን አስገብቼ ፀጉር የፈሰሰበት ጭኑን እነካከዋለሁ። ከደስታ ይልቅ ውስጤ የሚሰማኝ አነጣጥሬ ያለመውደዴ ቁጭት ነው። ታድያ እሱ እንዳይሰማኝ አድርጌ ወደ ውጭ እተነፍሳለሁ፤ እተነፋፈሴን ከሰማኝም የፍቅር ስራው ያረካኝ ለመምሰል በወዛም ፀጉር የተሸፈነ ፊቱን አፌን ከፍቼ እስምለታለሁ። ... ሳገባው ወድጄው ነበር። ውሸት አይደለም። አሁንም እወደዋለሁ። ግን አንድ ቀን ከቤቴ ልወጣ ስል ደጃፌ ላይ ይኼን `አስናቀ` የተባለውን ወጣት አገኘሁት። ደነገጥኩ። በሁለመናዬ።” [ገፅ፥ 83]

ሎሚ ሽታ አንሶላ ስር ድርጊትን በስሜቷ አሻሽታ፥ የመምሰልና የመሆን ጭንቀት፥ የልብና የአካል ትርታ፥ አብረው ተኝተው ባዳነት ደባልነት ሲነጣጥላቸው ጥቃቅኑ ይተረካል። በተራው ይህን ህይወት ታደሰ ሲተርከው በአንፃር ለውጥ ምክንያት ሰው እንደ መሰለው መፍረዱ ይኮሰኩሳል። የልቦለዱ ሃምሳው ገፅ በዚህ መልክ ዕዝራ

ፓውንድ እንዳለው፤ በአንድምታ የተለበለብ የቋንቋ ትርታና ንዝረት ነው። ጀርመናዊ ፈላስፋ ሾፐንሆር ያስተዋለው ለ“እቴሜቴ ሎሚ ሽታ”ትረካ ይስማማል። “The business of the novelist is not to chronicle great events but to make small ones interesting. “የልቦለድ ደራሲ ተግባር ግዙፍ ሁነቶችን መዘገብ ሳይሆን፥ ከትንንሽ ጉዳይ ጣዕም እየቀዳ መተረክ እንጂ እንደማለት። “ጊዜን ላንዳፍታ ቆም ማድረግን፥ ለማስተዋል፥ ለመሳቅ፥ ለመተከዝ ፋታ ማግኘትን የማይመኝ ማን አለ?” ብሎ ቢጠይቅም ሰሎሞን ዴሬሳ፥ የአዳም ረታ ብዕር ጊዜን ብቻ ሳይሆን ስሜትን፥ ምስልን፥ ኮሽታን፥ ትንፋሽ ጭምር በቃላት ዘለዓለምነት ይለግሳቸዋል። ሁሉአገርሽ የቤተ ክርስትያን ግድግዳ ስትደገፍ ምን ተሰማት? “በሚበርድ ጠዋት ግድግዳው ይሞቃል። በሃሳቤ ሺህ መላዕክት ግድግዳው ውስጥ ከሲሚንቶው ጋር ተገንብተው ጀርባዬ ላይ ሲተነፍሱብኝ ይታየኛል። ያስፈራል፤ እና በመደመምም ይሞላል።” የአዳም ረታ ልቦለድ ምናባችን እንዳይፈዝ ለህይወት ግለት ነው።

## *ክፍል 3*

በዚህ ልቦለድ ብቻ ተወስነን አዳም ረታ የመለመላቸውን ሴቶች ብናጤን፥ ምን ያህል ይመስጡናል? በተለይም ሎሚሽታ? ሶስት ውብ ወጣት ሴቶች -ምስራቅ፥ ሎሚሽታ እና ሁሉአገርሽ- የእንስትን የባህሪይ ሆነ የአኗኗር መልኮች በከፊል ይወክላሉ። ተነጥላ በራሷ መንገድ የተጓዘችው የአለማያ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ከነሱ ትለያለች። እንደ ጥላ ውልብ የምትል አዳም ረታ ከሌላ አጭር ልቦለድ የኈተታት ቀለመወርቅ አለች። [ለድልህ፥ ገፅ 177] “ከኈረቤታችን ከእትዬ ቀለመወርቅ በተቀር እቤታችን ቡና ለመጠጣት የሚመጣ አልነበረም። ብዙ ጊዜ ሳገኛቸው አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ ነው። እናቴ ሞታ ጨርቆስ ስትቀበር ያለቀስነው ሶስት ሰዎች ብቻ ነበርን። እኔ፥ ነፍስ አባቷና እትዬ ቀለመወርቅ።” ለዚች ሴት ደራሲው በሕፅን ወይም በግርጌ ማስታወሻ ለአንባቢ ሊገልባት ይገባ ነበር። ከሆነ ስፍራ ውልብ አለች እንጂ ታሪኳ ታፈነ። ለምን ከመንደሩ ሰው ሁሉ ተለይታ የምስራቅ ጓደኛ ሆነች? ትዳር መስርታ ልጅ ወልዳ የዩኒቨርስቲ ትምህርቷን ስትቀጥል፥ ከአንድ ከምታደንቀው ተማሪ ትማግጣለች። ቆይቶ ህሊናዋ ሲቆጠቁጣት ስራዋን ትታ የቤት እመቤት በመሆን ለባለቤቷና ለልጃቿ አገልጋይ ሆነች። ስለዚህ ምስራቅ ከትዳር ውጭ ባልጋለች ተብላ መታማቷ ሁለቱም እኩል የሚያቃስቱበት ሰቆቃና ምስጢራቸው አስተሳሰራቸው፤ ይደማመጣሉ። አዳም ረታ እንደ ጠልሰም ተጠቅልላ ከልቦለዱ የወሸቃት እንስት፥ እንደ ሰባራ ቧንቧ ልትፈስ ያደፈጠች ናት፤ ኈረቤት መባል ብቻ አድበሰበሳት።

ደራሲው ንቁ ተደራሲ፥ ጥቆማ የሚከተል አንባቢ ስለሚያደፋፍር ይሆናል በምልክት የቀነበባት።

አዳም ረታ ይህን ልቦለድ በምን ምክንያት ሊፅፈው ቻለ? ምናልባት “እቴሜቴ የሎሚ ሽታ/ ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ/ ምንም ምንም ምንም አላለኝ/ ትዳሩን ፈቶ ልውሰድሽ አለኝ” ይህ የህፃናት ዘፈን እሴቱ ከአዕምሮው ለአመታት እየተንጓለለ ፋታ ስለአልሰጠው፥ ለእያንዳንዱ ስንኝ ታሪክና ሁነት በምናቡ እየፈተለ ለልቦለዱ መነሻ ሳይሆነው አልቀረም። ሌላ ሰው ያወጋለት፥ ያነበበው ሳይሆን ከዚህ የሴት ህልም፥ ምኞትና ስጋት በትውፊታዊ ቅብብሎሽ ለዘመናት የተንከባለለውን አድምጦ ተደምሞ የፈለቀቀው ልቦለድ ይሆናል ነው ግምቴ። ይህ ደግሞ ብጣሽን ነገር ለብርቅ የፈጠራ ውጤት የማብቃት ልዩ ክህሎት ይሻል። በጣም ስስ ከሆነ ትልም/ሴራ ጥበባዊ ጥልቀት መጐልጐል የቻለበትን የአፃፃፍ ክህሎታዊ ንባብ ለጊዜው ገታ አድርገን በሎሚሽታ ሴትነት፥ ወሲባዊ ረሃብ፥ ረግረግነት፥ ስጋትና ፍላጐት እንደመም።

ሎሚሽታ ትዳሯን አፍርሳ ወይም ፈርሶባት ወደ አዲሱ ፍቅረኛዋ ጉያ መኮብለሏ፥ በማኅበረሰቡ ሴቶች መታማቷ እኩይ እንስት ሊያስመስላት ይችላል። ግን አይደለችም።

** ሀ **

ወሬ እወዳለሁ። ከሚያበላኝ ከሚያጠጣኝ ይበልጥ የሚያዋራኝን አቀርባለሁ።” [ገፅ፥ 77]

ሎሚሽታ ከታደሰ ጋር ትዳር ከመሰረተች አምስት አመት ቢሞላትም፥ በፍቅር የጀመረችው ግንኙነት እየጣማት ስራዋን ትታ ከቤት መዋል መርጣ ነበር። እየቆየ መሰልቸትና መሰላቸት፥ በዝምታ የተወረረ ጐጆ ውስጥ ማዛጋት ያቅበዘበዛት ይመስላል። ሴት ማንነቷ ተኮራምቶ የትዳር እስረኛ ሆና ስለምንም ጉዳይ መመሰጥ ስታቆም፥ ከባዳ ወንድ እግር መሃል ለኅላዌ ትርጉም ካፈላለገች፥ እንዴት ባለጌ ተብላ ትኮነናለች? ለዚህ ባዶነት ተጠያቂ ማን ነው? “ወሬ” ከእህል ከውሃ በላይ ከተነፈገችና እንደ አንድ መሰረታዊ ፍላጐት ከገነነባት የየዕለት ውሎዋ ድግግሞሽ ምን ያህል ቢጐመዝዛት ነው? መኖር እኮ ማንጋትና ማምሸት ብቻ ከተካው ለህይወት መቅበዝበዝ እንደ ካህን ትንቢት ከራቃት፥ አንሶላ የሚጋፈፋት እንደ ግለሰብ የተነፈገችውን የህይወት ንዘረት እያስተዋለ ካልደረሰላት፥ በባዶነት መታፈን እንኳን ጐጆ የሌላውን ነፍስ ለመናድ አቅም ሸሸጓል።

ትያትር፥ ጭፈራ ቤት፥ ዘመድ ጥየቃ … ውሰደኝ ብትለው ምናልባት በወር አንድ ቀን ቢተርፈው ነውና ምርጫዋ ከሰፈሯ ራቅ ወደ አለ ቤተክርስትያን መመላለስ ሆነ። አጃቢ ሴት እንዲቀጠርላት ጠየቀች። “… አንዲት ቀን እንኳን ማዕድ ላይ `በስመአብ` ብላ የማታውቀው ሎሚ `ቤተክርስትያን እስማለሁና አጃቢ ቅጠርልኝ` አለችኝ። አልተከራከርኳትም። ግን ውስጤ አድፍጦ የተቀመጠው የጥርጣሬ አውሬ የሚበላው እንዳገኘ ሁሉ እያዛጋ ተነሳ።” የትዳር አጋሯ ታደሰ፥ ከባዶነት ለመሸሽ የሆነ ጥግ ማፈላለጓን፥ ለመተንፈስ መቃተቷን አጢኖ የአናኗር ለውጥ ከመዘየድ ይልቅ ተንኮል ያደራ ጀመር። ብዙ ወንድ የቀማመሳትና በአባቷ ተግሳፅ የታቀበችው ጎረቤቷ ሁሉአገርሽ ነበር የተቀጠረችላት።

“… መጀመሪያ ጨዋ መስላኝ ነበር አጃቢ ስትፈልግ። … ሎሚሽታ ቤተክርስትያን የምትሄደውና የማይገባትን የግዕዝ መዝሙረ ዳዊት እየተውተረተረች የምታነበው ፍትወት የሚያቃጥላቸው ዘጠኝ ጐራሽ ዓይኖቿን ከጠርጣሪ ለመከላከል ሳይሆን አልቀረም እላለሁ። እንደ እኔ ነፃነት ቢኖራት ትንሽ ባለአንድ ቤት አልጋ ተከራይታ… `የአገሬ ወንዶች ሆይ! ኑና ሒሳቤን ሰጥታችሁኝ ወደ ምትሄዱበት ሂዱ` ብላ ትለጥፍ ነበር።” ሁሉአገርሽም ብቻነት፥ የትዳር ባዶነት ሎሚሽታን ማቅበዝበዙን ሳታመዛዝን ጋለሞታ ናት ብላ ፈረደች። ደራሲው አንድን እንቅስቃሴ ከሶስት ተራኪዎች አንፃር እያዛዟረ ሲተርክ እንመሰጣለን። ሎሚሽታ ውስጧ የታመሰውን ሳያስተውሉ፥ በአደባባይ ድርጊቷ ብቻ ለቀነበቧት የቅርብ ሰዎች አለመንበርከኳ፥ እንደ ምስራቅ አለመሰበሯ አንድ እሴቷ ነው። ከቤተክህነት መመላለሷ የበጃት ቢኖር ከሚመጥናት ወንዳወንድ አስናቀ ልቦና ውስጥ ለመንዘር እድል ማግኘቷ ነው እንጂ ለተለያዩ ወንዶች ቀሚሷን አልገለበችም፤ የሁሉአገርሽ ሃሜት የቅናት መሰለ። ለመኖር

መድፈር ብቻ ነው ሎሚሽታን ከባዶነትና ባዳነት የሚያስጥላት። ገጣሚ ዳዊት ፀጋዬ፥ ሎሚሽታን ተዋውቆ የተቀኘላት ያክል አገኘት።

ምን   ዐይነት ጨለማ ነው ልባችንን የከበበው?

ምን ዐይነት ድንዛዜ ነው ሕይወታችንን የወረረው?

ምን ዐይነት ድንዳኔ ነው መንፈሳችን ላይ የሰለጠነው?

እንዴት አይነት ልብ ነው፥ ማንስ ተብሎ ይጠራ?

መኖር የማይደፍር! መሞት የሚፈራ!" [አርነት የወጡ ሐሳቦች፥ ገፅ 59] ሎሚሽታ ተንቀሳቀሰች።

** ለ **

እምሳለምበት ቤተክርስትያን ሴቶች ረድፍ መጣና፥ ... እኔ ሴት መስሎኝ ጆሮዬን ሳውሰው ጠጋ ብሎ፥ በዚያ በሚያምር ጐርናና እንደ ዳምጠው መኪና በሚካበድ ድምፁ :-`እሰይ! ጠረንሽ እኮ የሎሚ ነው` አለኝ።

በእውነት ነው የምለው ድንግጥግጥ አልኩ።... ከአፍንጫው በስተቀር ፊቱን በምታምር ቀይ ጥለት ያላት ነጠላ ሸፍኗል። መሬት የሚያብስ የአገር ባሕል ቀሚስ ለብሷል።... ደጀ ሰላም የማይባል ለስጋዬ የጣፈጠ ዝርዝር ነገረኝ። ... ረኻም የሚጣፍጥ ልብ የሚያሸፍት ነገር በዚያ ደብዛዛ የዓመቷ ማሪያም ሌሊት እንደሚሞቅ የድምፅ ጣዝማ ነገር በጆሮዬ ቀዳዳ አንቆረቆረ። ... በተለወጠ አስመሳይ ሴተኛ አካሄዱ እየተንኳተተ እኔ ካለሁበት ቦታ ተነስቶ ሲሄድ በዕፍረትና በመገረም አየሁት። ባለቤቴ ታደሰ እዚያው ቤተክርስትያን ግቢ በወድያ በኩል ዛፍ ስር ቆሞ እንደ መልካም መሪ ጌታ በሁለት እጆቹ ዳዊቱን ፊት ለፊት ዘርግቶ ይዞ ያንቸለችል ነበር። አስናቀ ... ታደሰ አጠገብ ሄዶ ሲቆም አየሁት። መጀመሪያ አፈርኩ። ቀጥሎ ግን በአስናቀ ደፋርነትና ጮሌነት ተደስቼና ተገርሜ እተንበረከኩበት ቦታ ጉልበቴን እስኪያመኝ በሳቅ ፍርፍር አልኩ።" [ገፅ፥ 77-78]

አዳም ረታ ትረካውን የጀመረው መቋጫው አካባቢ ብቻ ሳይሆን ማንንም አንባቢ በሚያጓጓ ልዩ ትዕይንትም ነው። የእመቤታችን ንግሥ ዕለት ሎሚሽታ ተንበርክካ፥ ታደሰ ዳዊቱን ዘርግቶ ለመንፈሱ ሲያደባ፥ ሁሉአገርሽ ምናልባት በድባቡ ተወስዳ ማሪያምን ለሆነ ጉዳይ ትማፀናት ሳለች፥ ከበዓሉ ከንግሡ ከመንፈሱ የላቀ፥ በህልሙ ለሎሚሽታ የሚባንን፥ ፍትወታዊ ፍላጐት የተጠናወተው ወጣት ድንገት ተላወሰ። ልቦለዱን ስናነብ ይህ ትዕይንት ከሶስት አቅጣጫ ተቀርጿል። አስናቀ፥ ሁሉአገርሽ እና ሎሚሽታ እንደ ስሜታቸው አስተውለውታል። ሁሉአገርሽ በአካል ገሸሽ ብትልም ትዝብቷ ግን ጠባብ ነው። ለፍቅር፥ ለአካል ውበት የመንገብገብ ኃይል ሰውንና እግዜርን ሳይፈሩ እስከ ደጀ ሰላም የመለጠጥ ድፍረት ሰብዓዊ ጥያቄ አልጫረባትም። ሎሚሽታ በባለቤቷ ተበድላ ይሆን? ፍቅር ተነፍጋ ይሆን? ለሌላ ተባዕት ወከክ ተርከክ የምትልበት ምክንያት ምንድነው ብላ ለማመዛዘን አልጣረችም። ሰው ገበናው ውስጥ የተሸሸገ፥ ሥነልቦናው የተሰነጣጠቀ ለመበርገግ አንድ ኮሽታ፥ ለመፈወስ እፍኝ ፍቅር የሚለማመጥ ውስብስብ መሆኑን ለመረዳት ያዳግታታል። ንቃተ-ህሊናዋ መንጋዊ ነው፤ በማኅበረሰቡ የጥሩና የመጥፎ ድንጋጌ ስለተወረሰ እንደማንም ተራ ነው ፍርዷ። "አስናቀ የምትለው ያ ጥቁር ልጅ ደጀ ሰላም ሊያያት ሲመጣ እንደማያውቅ ...ገሸሽ ብዬ የቤተክርስትያን ግድግዳ ተደግፌ ቆሜአለሁ። ... እንዲያ ግርማ የሚያደፈርስ የማይሆን ነገር ደጀሰላም ውስጥ ያደርጋል። ...አስናቀ ሎሚ ሽታን እየተንፏቀቀ ሲቀርባትና ሲያንሾካሽኩላት የተረጋጋ ዓይን ያወጣ ፈቃደኝነቷን አየሁ።" እያለች ሁለቱን ታጠላላለች።

ሎሚሽታ ከአስናቀ ቀጠሮ አልነበራትም። ተንበርክካ መንፈሷን ለእግዜር አደራ ስትሰጥ ወይም -ጥብቅ አማኝ ስለአልሆነች- ከምናቧ የሚርመሰመስ ስጋት ሆነ ተስፋ አስደምሟት ሳለች፥ እንደ ሴት ለብሶ ድንገት ከመንፈሳዊ ድባብ ያባነናት አስናቀ ነው። የሴትነት ኩራቷን፥ ገና ውብ መሆኗን ያረጋገጠላት እንቅስቃሴ ብቻነት ያፈዘዘውን ልቦናዋን ነፍስ ዘርቶበታል። አስናቀ ይህን ገላ፥ ይህን ውበት ለማጣጣም አላቅማማም። የ "የፍቅር እስከ

መቃብር" በዛብህ፥ ሰብለወንጌል ዕቃ ለማውረድ ስትንጠራራ በቅርጿ ተርበተበተ እንጂ መች አፈፍ አድርጐ ገላቸው እኩል ነዘረ? የ "አደፍርስ" አብይ ገፀባህሪ ሮማንን ከህልም ወደ ተግባር ለማሻገር አቅም አንሶታል። አስናቀ ግን የማርያም ንግሥ ዕለት፥ ማኅበረሰቡ ለስለት ለፀሎት ባደገደገበት ምሽት፥ እሱ ለፍቅር አባዜ ማርያምን ምዕምናንን መኖራቸውን ዘንግቶ ሰብሮ ገባ። በአማርኛ ልቦለድ ያልተለመደ መቼት ነው፤ ስንቱ ለነፍሱ የመንፈስ ምስጢር ሲያባብል፥ ሥጋዊ ነገር እየከነከነው ሲፀልይ፥ አፍቃሪ እንደ ሴት ተሸፋፍኖ ሎሚሽታን ተሻሻት፤ ደጀሰላም የፍቅር ደብዳቤ ተለዋጭ ዘይቤ ሆነ።

ታደሰ የተለበለቡ ትናንቶቹን፥ህመሙን ከሎሚሽታ ሸሽጐ፥ ለሥነልቦና ቀውሱ መታከም ሲኖርበት እንደ ጤነኛ ሰው ከቤተክርስትያን ዳዊት የሚደግም እየመሰለ ባለቤቱን በሚስጥር ይቃኛት ነበር።

" አጃቢ ቅጠርልኝ ካለች በኋላ ከስራ እየቀረሁ ባልጠረጠረችኝ ጊዜና ቦታ ሰለልኳት። ከማን ጋር እንደ ዋለች አየሁ። ... እያንዳንዷን ገጠመኝ ማስታወሻዬ ውስጥ በዝርዝር አሠፈርኩ። ... እኔ ቤተክርስትያን አንድ ቀን አብሬአት ሄጄ ራቅ ብዬ ስቆም አስናቀ የተባለው ጐረምሳ ወዳጇ አጠገቧ ሴት መስሎ መጥቶ ሲቆም እኔ ጋም ተጠግቶ ሲያሾፍብኝ ምን የሚያስቅ አለ? ... የመራቅ ድርጊቷን ባልገባት ግን በረቀቀ መንገድ ራሴ እየደገፍኩ እልህ ሁሉ ገብታ ፈጥና እንድትሄድልኝ ገፋፋኋት።" [ገፅ፥ 123-124]

ለአምስት አመታት እንደ ገረድ እያገለገለችው፥ ብቻነት መሰልቾት እስኪበልዛት ድረስ ተኮማተረች። ከአቅሟ በላይ ሲሆን ለአደባባይ የቋመጠችው ሎሚሽታ፥ ትኖር የነበረው ወጥመድ ውስጥ መሆኑ ይሰቅቃል። ይህን አለማወቋም አያዋነቱ፥ ማኅበረሰቡ እሷን እንደ ሴሰኛ፣ ታደሰን እንደ ሰለባ መፈረጁ የከፋ ነው። የሚኖሩት የጋራ ህይወት ዘመም ሲል፥ ለትዳሯ ብላ ብርቅ አምስት አመታት ማባከኗን ሳያመዛዝን፥ አይኖቿ ወንድ ፍለጋ ለምን እንደተቅበዘበዙ ሳያስብበት አድብቶ ጉድጓድ ማሰላት። ለምን ምርር ብሏት እንድትኮበልል መንገድ ጠረገላት? እሷ ህሊናዋ እየወቀሳት፥ ጉረቤት እያማት፥ እሱ ጥፋተኛ ሳይመስል እየታዘነለት በዳይና ተባዳይ ቦታ የመለዋወጣቸውን ማኅበረሰባዊ ድፍረት ደራሲው በድንቅ ትረካ አፍርጦታል። ማኅበራዊ ፍርድና አቋም ግለሰብን አለአግባብ ሲዳጨው ጉዳቱ የከፋ ነው።

የገላዋ ውበት አልያም ወሲባዊ ጣዕሟ ፍቅር የሚያስይዝ፥ አስተሳሰቧ ግን የሻሸረ ከንቱ ሴት ለታደሰ ወይም ለአስናቀ ሳይሆን ለሚያውጠነጥን ተባዕት ፍዳ ናት። ደበበ እነሎሚሽታ እየታወሱት በ"ቅዠት ... ቅዠት" ግጥሙ ተቀኝቷል። "ፈገግታውን በመስቷት እያስተካከለ፥ ሌላ ቋንቋ ባይገባት፤/ እንደማንም ናትና እንደማንም ያባብላት?/ ልዩነቱን ይረደዋል/ መደዴነቷን ያውቀዋል።/ ልቧን ገልጦ ያየ ሲመስለው/ ቤህ ነው እሚሣቀቀው። / ተስፋ እሚቆርጠው።/ ይሁንና አፍቅሯታል፥/ ተራነቷ ሳይጠፋው፥ `ልዩ` ናት ሲል አምልኳታል። /...... / ግን ሀክ ብሎ ላይተፋት/ ነብሱ ውስጥ ተሸንቅራ/ ተቀርቅራ።" [ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ፥ ገፅ 25-26] አዳም ረታ ከጡት መያዣ ሥር የተወሸቀ ብጣሽ ክር የሚያርገበግብ የቋንቋ ምትሀት በጀው እንጂ የተመለመሉት ሴት ገፀባህሪያት አስተሳሰባቸው የእንስት ተራነት ይመሰክራል። የማኅበረሰብ ድንጋጌ፥ እምነትና ጭቆና ውጤት በመሆናቸው ዛሬም ተኳኩለው ሞባይል ቢወለውሉም በአመዛኙ ፍዝ ናቸው። ግን እንደተወርዋሪ ኮከብ በብርሃን ምናባችንን የሚሰነጥቁ ሴቶች የተፍታቱበት፥ በደራሲው ብዕር የገነኑም አሉ።

ሴት ብሎም ወንድ ተራ ወይም ጥልቅ መሆናቸው አይደለም አዳም ረታን እንቅልፍ የሚነሳው። ተረክ ማነፅ፥ በትረካ ፍጥነት፥ በባህል ሆነ በአስተሳሰብ ተጋፊ ሁነቶች ጊዜን መስፈር፥ በቋንቋ ምጥቀት ደቂቅና ግዙፍ ድርጊቶችን ማንጠፍጠፍ እንዴት የኅላዌን ማቃሰት ሆነ መቦረቅ ኮሽታውም ቢሆን አንባቢን ማስበርገጉ ነው ለብዕሩ ንዝረት።

***ክፍል 4***

"ወደዚህ ሃሳብ (ተነካናኪነት) እንዴት መጣሁ? ... የአንድ ደራሲ ወዳጄ ጎረቤት ነበረች። ...በውበቷ ተማርኬ ነበር። ገና ሳያት ፍቅር እንደያዘኝ ገብቶኝ ነበር።`የሚበላ ትፈልጋለህ` አለችኝ። ...ቆንጆ ስትጋብዝ እምቢ ይባላል? አይባልም። ...ኩላሊት ጥብሴን አንዴ እንኳን በእጄ ሳልነካ እንደ ትንሽ ልጅ እሷ እያጐረሰችኝ ጠግቤ በላሁ። ስሰናበታት ያጐረሰችኝ እጇን ከነለበሰው መረቁ አገላብጬ ሳምኩት። ጣቶቿ ዛሬ ድረስ ለእኔ የፍቅር ምንጮች ናቸው። ቅርባዊነት ወይንም ተነካናኪ የመጣው ከዚያን ቀን በኋላ ነው።" ["መች ትመጣለህ?"፥ ገፅ15]

ስለ ኪነጥበብ እንዲህ የረቀቀው ሰዓሊ መስኮት ገረሶ በ"እቴሜቴ" ልቦለድ የታደሰ አባት ዘመድ ነው። የአዳም ትረካዎች በመቼት፥ እሳቦት ወይም ገፀባህሪ ስለሚነካኩ a novel of short stories የአንድ አብይ ልቦለድ አጭር ትረካዎች ሆነው ይነበባሉ። እያንዳንዱ ትረካ ብቻውን ሙሉ ነው፤ ከሌሎቹም የተነካካ የተያያዘ እንጂ ባዳ አይደለም። <እቴሜቴ ሎሚ ሽታ> የሰባት ትረካዎች ስብስብ ሲሆን በሂሳዊ ቅርበት የተነበበው አንድ ብቻ ነው። የተቀሩት ስድስቱ እኩል ይመስጣሉ። የሚነካኩ ድባባቸውም የተቀላቀለ ሆነው ሳለ፥ አንዱን ብቻ ማንበቤ አዳም ረታን ሳልበድለው አልቀርም፤ ሰባቱን በጥሞና መገምገም የሚያመቸው በመጽሐፍ እንጂ ለጋዜጣ እንደ ጥቆማ ነው። "መች ትመጣለህ?" ትረካው የመከጀል የመውደድ ጉዳይ ቢሆንም የፉጨት ቅኔ፥ ለቀጠሮ ያልበቃ ቀናት ያፈዘዙት፥ ግን በሌላ ወቅት ሊደመጥ የሚበቃ። "በከንፈሮቿ ልትለቀው ወይም ልታስቀረው (እንደ ሞናሊዛ) የምትሞክረውን ፈገግታ በአይኖቼ ቆንጥጬ ያዝኩ" እያለ ወጣቱ ይደፋፈራል። "ከአፏ ላይም ለሆነ ማታ የሚሆነኝ ቅዠት ልለቃቅም" ግማሽ ሰዓት ምልክቱን እያፏጨ ቢጠብቃትም ፍቅረኛው (የምስራቅ ጓደኛ የቀለመወርቅ ልጅ) ከግቢዋ አልወጣችም። ጐረምሳው ፍቅረኛውን ግንብ ስር ቆሞ ሲጠብቃት የሎሚሽታን ባል ያስተውላል። "እወድያ ወደ ግራ የሚያልፍ አሮጌ ፔዦ ተሰብሮ ሞተሩ ይጨሳል። ባለቤቱ ጠበቃው ታደሰ ፍቅረ ስላሴ ነው። የሚጠብቀው ነገር እንዳለ ሁሉ ወገቡን ይዞ ወዲያ ወዲህ ይላል። ያቺ ቁሊ ሚስቱን ሎሚሽታን ጐረቤታችን አስናቀ ወስዶበታል ይባላል። አንዳንዴ ሲበሳጭ በመኪናው ይሁን በሚስቱ ዝም ብሎ ወገቡን ይዞ ወድያ ወዲህ ይላል" [ገፅ 20] ሰው ሌላውን (ያውም የጐረቤት ቅርበትና አብሮ መኖር እያለ) በሽፋኑ ሲፈርድበት የግንዛቤ መዛባት ነው።

ሁለተኛው ትረካ "የስብሃት ጢም" ጥልቀቱ አያበቃም፤ ደጋግመው ቢያነቡት አዲስ ይሆናል። "ቤቱ ውስጥ ቀዝቃዛ ግራጫ ጨለማ ነበር። የሚነቃነቅ የሚመስል። ትንሽ እንግዳ የመሰለ፥ ማለት ከሌላ ቦታ ተጉዞ ለትንሽ ቀን ለማረፍ እዚያ ገብቶ የሠፈረ። እንቅልፍ እምቢ ስላለውም ስብሃትና ፋኖስ ዙሪያ የሚበሉትን እየቀላወጠ የሚንገላወድ ትርጉሙን የደበቀ ጨለማ፥ የብርሃን ነጠብጣብ የወደቀበት ግስሌ ጨለማ።" ትዳር፥ ውበት፥ ፍቅር፥ ወሲብ፥ ጥበብና መለያየት ... ሰውን በርብሮ የማወቅ አቅም አለው። ልዩ ሃይል አለው፤ ቅኔያዊ ገለጣ ብቻ ሳይሆን የሚሰረስር ጥልቀትና ትካዜም ነው። ከህይወት የመጠቀ ግርማነት የፀደቀበት። ድባቡና የሰዓሊ መስኮተ ገረሶ መኖር ከሎሚሽታ ያነካከዋል። ስዕል መሳል ከጠጠር መጣል ጥንቆላ ጋር ቢመሳሰልም ጎላዌ እስከ አስማታዊ ዕውነታ -magical realism- ተለጥጦ ያስቃትታል። "ለድልህ" ፍቅር፥ ክህደት፥ ወሲብና መቀማማት፥ ፀፀትና መስዋዕት፥ የትዝታ ስጋት የአዳምን ብዕር በሚያስመልክ ሁኔታ ገመናን የሰረሰረበት ቅኔው ነው። "... ከእስር ቤት በፊት የሚያውቃት የመጀመሪያ ወዳጁ ከዐሰል (ማር) የተፈለፈለች የምትመስል አደሬ ልጅ ናት። ወደ መርካቶ የቅመምና የቅራቅንቦ ሱቋ ስትጓዝ ከኋላዋ ወለላ እየተንጠባጠበ የሚቀር፥ የሐረር ነጋዴና የድሬደዋ ተማሪ አረንጓዴ ምላሱን ጐልጉሎ የሚከተላት ዱብራ።" በሎሚሽታ ልቦለድ ለታደሰ እናት ጓደኛ የሆነችው ቀለመወርቅ፣ ልጇ ካሌብ ያፈቀራት እምቡጥ ናት፤ አዳም ረታ በብዕሩ ውበቷን የመጠጠው። ቀለመወርቅ ከትዳር ውጭ ብትማግጥም ከሰው ጋርደዋለች፤ ምስራቅ ግን ሰለባ ሆና ባከነች። ቀለመወርቅ በየዕለቱ ከምስራቅ የማትለየው የሷም ዕጣ ሊሆን እንደሚችል ስለተገነዘበች ነው።

"አፉን ከፍቶ ሊውጣት የሚቁነጠነጥ ፀጥታ። ይኽን እንደ መጅ የሚከብድ ፀጥታ በጐሪጥ ታየዋለች። ... ቃሪያ እየዘገነች በዝምታ ሙቀጫ ውስጥ ትከታለች። ሙቀጫው ሲሞላ በፈገግታ በሚሰባበሩ አይኖቿ ካሌብን

እያየች በቀስታ ቃሪያውን መሸክሸክ ጀመረች። አሁን ልጇ መናገር ወይ መጠየቅ ቢያቆም ትወዳለች። ወደ ምትሸሸው እንዳንድ ነገር በጥያቄ እየጐተተ፥ በቀስታ እየነዳ በልጅነቱ ቅንነት ወደ ማትፈልገው የቁጭት ኩሬ ዳር እንዲወሰዳት አልፈለገችም። መረሳት የሚገባቸው ነገሮች አሉ።" ቀለመወርቅ ማኅበረሰቡ እንደ ምስራቅ ባያገላትም ህሊናዋ በቋፍ ተርገብግቦ ቀረ። "ሁለት ተኩል የውስጥ ሱሪዎች ለአዲስአባ" የሚመስጥ፥ ከከበዱ በኋላ ከልጅነት እስከ አዋቂነት የኖሩትን ፍቅር፥ ጭን፥ የትምህርት ቤት ትዝታና የእንስት ሙታንቲ ታሪክ እያንጠፈጠፈ ተሰጥቶበታል። ከየዋህነት ወደ ብስለት ጉዞ ነው። ለጭን ወርቅና ሰም ነው። ማርታ "ዕርጥብ እግሮቿን ነጠላ ጫማ ውስጥ አስገብታ እየተሳበች ሔደች። ወደ ሰማይ የምትነሳ ትመስላለች --በነፋስ እንደሚገለብ የተሰጣ ጨርቅ። የቂጥዋ ክብ ቀሚሷን ነፍቶት ገና ከምጣዱ የወጣ ሴት አኩሪው ያልተገፈፈ ሙልሙል ያስታውሳል። ከሁለመናዋ የሴትነት ወላፈን ይነሳል። የምትነቃነቅ አስማት ናት።" ለዚህም ነው ሁለት ተኩል የውስጥ ሱሪ የተባለው። የ "ለድልህ" ልቦለድ ቀለመወርቅ ብቅ ትላለች። ሎሚሽታም ስትንቀሳቀስ እናገኛታለን። ተራኪው ደራሲ ነው። "እንዲህ የሴት ጭን የሳበኝና የማርታን (ባለቤቱ) የልጅነት ጊዜ አቅርቦ ያስጨነቀኝ አጋጣሚ ነበር።" መጽሐፉን ከምታደንቅ ሎሚሽታ ጋር ይተዋወቃል። " … እያዋራችኝ ዐይኖቼ በድንገት በግማሽ የተራቆቱ ጭኖቿ ላይ አረፉ። … የጭኖቿ ርዝመት ልስላሴና ጤነኛነት ልቤን ወሰደው፥ ባለትዳር መሆኔን ረሳሁ። … ስትወርድ እሷን ለማሳለፍ ቀድሜ መውረድ ነበረብኝ። ከታክሲው ለመውረድ ስትጣጣር እነዛ የሚያምሩ ጭኖች ተከፋፈቱ፥ የፀሐይን ብርሃን ተቀብለው አስካሪ ቀለም አወጡ፥ ዐይኖቼን ከእነሱ ላይ ማንሳት ከበደኝ። … ልትሰናበተኝ ስትጨብጠኝ ገላዬ እንደ እሳት መንደድ ጀምሮ ነበር። ምራቄን መዋጥ ተስኖኝ ነበር። ሰላም ብላኝ ከሄደች በኋላ አካሄዷን አየሁ። ታክሲ ውስጥ ተመልሼ ስገባ ሁለመናዬ እየነደደ ፈለግኋት።" ለውበቷ ወንድ በደከመ ቁጥር ማኅበረሰቡ እግዜር ለማሳሳቻ ነው ያስቀመጣት እያሉ ያብጠለጥሏታል።

ምናልባትም ከርዕሱ ጀምሮ ለሴት እንግልት፥ ለዘመኑ ወጣት ብክነት እስከ የልቅ ፊልም ጣጣ የተተረከበት ነው "… የመጨረሻዋ የቀበሌ 01 ድንግል"። ይህ ትረካ አዳም አለወትሮው የተለጠጠበት ነው፤ በተለይም አብረሃም የነፃነትን ድንግል ለመግሰስ የተንዛዛበት ጉዞ መከርከም ይሻል። ቢሆንም ተታላ - ለፍቅር መስሏት- የልምድ ማነስ `ልጃገረድነቷን` ለጉራ ከወሰደ በኋላ ከቁጭት ለመላቀቅ ጊዜ ይፈጅባታል። ይልቅ ጣዕምና ለዛ የሰጠው የእናት አባቷ ታሪክና ሁኔታ ነው። በሌላ አጫጭር ልቦለዶች የተቀረፁ እዚህ ገጠመኞቻቸው እንደ ክር ይመዘዛል። የትረካው አንፃር በሁሉን አወቅ እና በልጅቷ አንደበት መተካካት አበልፅጎታል። "እና አንድ ቀን ጉድ አየሁ። ያውም የሚያሳዝን። የክርስትና እናቴን ልጅ ጋሼ ገዳምን መርካቶ አስፋው ሆቴል በጀርባ ከዛች ቁሌታም ሎሚሽታ ጋር ተከታትሎ ሲገባ። መጀመሪያ ለብቻቸው ያሉ ያልተለያዩ መስሎኝ ነበር። … ድ`ሞ የእሱ እየተገላመጠ ማየት። ጠርቼው ሰላም ልለው ምንም አልቀረኝም ነበር መጀመሪያ። ሳያዩኝ ተከተልኩዋቸውና እዛ ሆቴል ግቢ እውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘው አየሁዋቸው። እጢዬ ዱብ አለ። ተደበርኩ። ለማንም አልነገርኩም። ሚስቱ ማርታ ይህን ብትሰማ ወይ እሱን ወይ ራሷን ትገላለች። አዘንኩ። ከዛ ትንሽ ሳስብ ማርታ እንዲህ ጀምራስ እንደሆነች አልኩ። ልክ በዚያች ደቂቃ ይሄን ባየሁበት ጊዜ ስንት መከዳዳት አዲስ አባ ይሰራል? አልኩ። ማርታ በጣም ቆንጆ ሴት ናት። ዛሬ እንኳን አራት ወልዳ በመንገድ ስታልፍ ጐረምሶች ወሬአቸውን አቁመው ዞር ብለው ያዩዋታል።" ትረካዎቹ ውስጥ ለውስጥ ተጠላለፉ። ከአንድ ስፍራ አበቃ የተባለ ከሌላ ልቦለድ ያንሰራራል --ልክ እንደ ሎሚሽታ ታሪክ። የተለያዩ ትረካዎች ቢሆኑም እንደ ጭብጥ የወንድ የሴት ገመናዊ ግንኙነት ያቀራርባቸዋል፤ መፅሐፉ የአንድ መንደር አውድ ወርሶ ገፀባህሪያት ሲተላለፉ ይነካካሉ። አንዱ ስለ ሌላው የሚያውቀው ነገር አያጣም።

ስለዚህ ባለታሪኮች ከመቼታቸው ተቀንብበው አልቀሩም። በአንደኛው አብይ የነበረ ገፀባህሪ በሌላው እንደ ንዑስ ይቀጥላል። ድንገት ከሌላ ልቦለድ ወደ አዲሱ የሰረጉት (እንደ ቀለመወርቅ፥ ሰዓሊ መስኮት) በአውዳቸው የነዘሩበት ህይወት አንባቢ ለማስታወስ ከበቃ ነው ብልጭ ድርግም በሚሉበት አፍታ ለመቼቱ እሴት፥ ለትርጓሜው ጨረር የሚለግሱት። ከተዘነጉ ለትረካው የሚያጐድሉት ጣዕም አለ። መጠላለፋቸው ግን ሸንቁር

አያበጅም። የሎሚሽታ ምጥን ልቦለድ የግለሰብ ህሊና ሆነ ስክነት እስኪደፈርስ፥ ማኅበረሰቡ አንዱ ሌላውን ሲያማ፥ በተለይም እንስቷ ለእንግልትና ለአንፃራዊ ደስታ መጋለጧ አስደምሞን አንብበነዋል። ከኅላዌ አውድ ቅልጥም የሚያክል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ነፋስ እንዲሚያስጋልባት እፉዬ ገላ፣ ጥቃቅን ክስተት በአዳም ረታ ምናብና ረቂቅ ቃላት ነፍስ ዘሩ። ትርምሱ፥ ደባው፥ ሽሹቱ፥ ቅኔያዊ ገለጣው፥ የትረካው ውበትና ውጥረት፥ ይህ ሁሉ በምን ምክንያት እንዲህ ታመቀ ብለን ስናስብ ይደንቀናል። መንፈሳዊ፥ ጥበባዊ ወይም ለሆነ የቁስ ክምችት ፍልሚያ አይደለም፤ ርዕይን ላለማስነጠቅ እድሜንና ሰላምን የመገበር እልህም አይደለም። ለዚህ ሁሉ ውጥንቅጥና ፍጥጫ ሳቢያው ለሰው አስፈላጊ የጣዕም ረሃብ “የወሲብ  ጉዳይ” መሆኑ ያስበረግጋል። ከታደሰ እናት እስከ ሎሚሽታ ቅዠት ማኅበረሰቡ የታመሰው ሴት በትዳር አጋሯ ላይ ከሆነ ወንድ ጋር መተኛቷ አንገብግቦት ነው። ግለሰብና መንደርተኛው በአንኳር የህይወት ጥያቄ፥ ለመለወጥ በመታከት ጉዞ ላይ ሳይሆን የተጠመዱት ከሴት ቀሚስ ስር ባለ ተረት መሆኑ ይመራል።

አዳም ረታ የነገረ ወሲብ ጉዳይ ግለሰብን የሚያስቀውስ፥ አንድን ቀበሌ ሥራ የሚያስፈታ አባዜ ብቻ ሳይሆን፥ በቀር ባህል የተተበተበ ማኅበረሰብ የግለሰብን ነፃነት ከመጋፋት ባሻገር ብኩንና አስተሳሰበ ጠባብ ትውልድ መቀፍቀፉን ኮንኖበታል። አልሰበከም፥ አልፈረደም ፤ በፈጠራ ድርሰት አንባቢን አስደመመ እንጂ። <እቴሜቴ ሎሚ ሽታ> ሌጣውን ነው እንደ ኖቬላ የተነበበው። ሤራው ወይም ትልሙ የሳሳ ቢሆንም ከድርጊት ይልቅ ሥነልቦናዊ የግለሰቦች ህይወት የተጐለጐለበት በመሆኑ ድንድኖአል። አዳም ረታ ጠፍጣፋ ልሙጥ የመሰለንን ሁነት በምናቡ እየላጠ፣  ከስሩ ያንቀላፋውን ኽንጉርጉርነት እየነካካ መስጦናል። የቋንቋ ችሎታው በፊደልና በፊደል መካከል እኛ ባዶ ነው  ያልነውን የሆነ ነፍሳት ሲርመሰመስበት እስከ ማስተዋል ይረቀል። ደቃቅ እንቅስቃሴ ወይም ፍዝ ስሜት አራግቦ ፍም ሲመስሉ እንደነዝዛለን፤ እያንዳንዱ ቃል ጫፉ ጣት ያበቀለ ይመስል በመዳሰሰ አዳም ትክኗል። ቋንቋው በኅላዌ ፍትወት ይንዘፈዘፋል። ዝነኛው ፈረንሳዊ ደራሲ Flaubert ስለ ቋንቋ ያጤነው ትርጉሙ አሻሚ ነው። “The human language is like a cracked kettle on which we beat out a tune for a dancing bear, when we hope with our music to move the stars.” [በሙዚቃችን ከዋክብትን ለማንቀሳቀስ ተስፋ ስናደርግ፤ የሰው ቋንቋ የተሰነጣጠቀ የነሀስ ጀበና ይመስላል። እንደ ከበሮ መታ መታ ስናደርገው ለደናሽ ድብ ቅኝት ይደመጣል።] ከመግለጥ ባሻገር አውሬን የማስደነስ አቅሙ፥ ቋንቋ ድፍን ብቻ ሳይሆን ፈረካሊከስ የተሰነጣጠቀ አካል መመሰሉ ምትሀቱን አይነፍገውም።

እንደ አንባቢ ሁሉም ገፀባህሪያት ሲናገሩ፥ ሲተርኩ ዘይቤያዊ ገለጣቸው፥ ጥቃቅን የተፈረፈረ የህይወት ትንፋሻቸው ይመስጠናል። ምስራቅ፥ ሎሚሽታ፥ ታደሰ፥ ሁሉአገርሽ ንግግራቸው እንደ አስተሳሰባቸው መጠን ቢሆንም፥ ሁሉም እንደ ባለቅኔ በረቀቀ ቋንቋ ነው የሚናገሩት? ደራሲው ተራ ቋንቋ መጠቀም ተሳነው ወይ? ሎሚሽታ ከአስናቀ ቤት ኮብልላ በርቀት የባሏን ቤትና ህይወት ታጠናለች።

“ከተከፈተ አፊ የሚወጣው ማንንም የማረከ ሞዛርት ነው። … አስናቀ አንገቴን ይልሳል። በጆሮዬ የወንድ ቀረርቶ ይሰዳል። ውስጤ የሚፋጅ ሐምሌ ነው። ምላሱ ቅባት የነካ መቀነት ነው ታጥቄው የማድር። … ጠበቃው ባሌ ደንገዝገዝ ባለ ምሽት ያቺ ልጅ ቤት ሲሄድ አየዋለሁ። ተንከራፎአል። የደከመው ይመስላል። … መንደሬ ጨለመ። ትዝታዬንም በረንዳው ላይ ጥዬው የእንጦጦ ትንፋሽ እንደ ወረቀት ገልጦትና ገልቦት እንዲሄድ።” ይህን የረቀቀ ቋንቋ መሽጐባት እንዴት የሎሬት ፀጋዬ ግጥም ይጐመዝዛታል? “መሽ እንግዲህ አምባ ልውጣ አለ ሰውየው። ይኼ ታደሰ ማታ ማታ ላንብብልሽ እያለ ጆሮዬ ላይ ከሚወረውርብኝ ስራ አጦች ከቸከቸኩት ነገር የማስታውሰው ነው።” ደራሲው ነከሰበት፤ የባለቅኔን ቋንቋ የሚያደናግዝ ችሎታ እያንዘፈዘፋት የ “እሳት ወይ አበባ” ግጥሞች ማጣጣም ሲሳናት ተዛነፈ።

በበዓሉ ግርማ “ከአድማስ ባሻገር” የአበራ ወንድም፥ እናቱ፥ የወንድሙ ሚስት ሲናገሩ ሲያወጉ ከረቀቁት ሀይለማርያምና አበራ ይለያል። John Foweler “The Collector” አንድ ተባዕትና አንዲት ሴት ናቸው ገፀባህሪያቱ። ወንዱ የባንክ ሰራተኛ ነው፤ ለቁጥር እንጂ ለቃላት ፍዝ ነው። ወጣቷ የስዕል ተማሪና ለኪነጥበብ

ነፍሷ ይርገበገባል። በውበቷ ተማርኮ ይጠልፋትና ገለል ካለ ቤት ውስጥ ያስራታል። እሱ ሲተርክ ሲያውጠነጥን በሚወክለው ዝርው ቋንቋ ነው። እሷ የየዕለት የእስራት ውሎዋን፥ ነፃ በነበረች ጊዜ ትዝታዋን ትፅፋለች፤ ዘይቤና ረቂቅ ነው። ይህን የመሰለ ሁለት ሶስት አንደበት በ <እቴሜቴ ሎሚ ሽታ> አይደመጥም፤ ሁሉም ባለቅኔ ናቸው። በሰባት ትረካዎች እንደ ህፅን ወይም የግርጌ ማስታወሻ ትረካውን ያበለፅገዋል። በተለይ በ "ለድልህ" እና "በሁለት ተኩል..." ድንቅ ነው። የሎሚሽታ ትረካ ግን መደምደሚያው ላይ [ገፅ 118] የተሰገሰገ የግርሬ ማስታወሻ ነው።

ታደሰ "ወደ ጠቅላላ ዕውነት የሚያቀርብ እርካታ ፍለጋ ወደ ግጥምና ንባብ ወደ በሰለ ኪነት ማጋደል" ጀመርኩ ቢልም አያሳምንም። ህግን ታክኮ ስለ ስዕል ከግርጌ የጠቀሰው የደራሲው ፍላጐት እንጂ ሥነልቦናው የታመሰ፥ የእናቱ ሰቆቃ የሚመዘምዘው፥ ባለቤቱ ሎሚሽታ ትዳሯን አፍርሳ እንድትኮበልል መንገድ የጠረገላት ታደሰ ስለሌላ ጉዳይ ቢያውጠነጥን እንጂ እንደ ሰከነ እንደ ተረጋጋ ግለሰብ የኅላዌን ጀርባ አይቀዝፍም። ልቦለዱን ዘመም ያደረጉት ሁለት ምክንያቶች (ሁሉም ገፀባህሪያት ከቅኔ ወንዝ መቅዳታቸው፥ የታደሰ ንግግር ሆነ አስተሳሰብ ብዙም ከሥነልቦናዊ ጭንቀቱ አለመጣጣሙ) ተረጋግቶ ልቦለዱን ለሚገመግም ካልሆነ እንደ ድክመት አይስለመለሙም።

አያዎነቱ ያጋደለው ጠገጉ እንኳን ሲመሰጡበት የሚጥም ፅሁፍ ነው። Milan Kundera ስለ ልቦለድ የተናገረው ትዝ ይለኛል። "All great works (precisely because they are great) contain something unachieved" የልሂቃን ትልቅ የጥበብ ውጤት የሚመስጠን፥ የሚያነቃቃን በሰመረላቸዉ ፈጠራ ብቻ ሳይሆን፥ ሞክረዉ አልሰበሰብ ባለዉም ምናባቸዉ ጭምር እንጂ እንደማለት።